# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የኮቪድ
# የኪራይ እፎይታ ፕሮግራም

**ማጠቃለያ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ [Montgomery County Department of Health and Human Services] (DHHS) በCOVID-19 ወረርሽኝ ተያይዞ ገቢ በማጣት ምክነያት የቤት ክራይ በጊዜው መክፈል ላልቻሉ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የቤት ክራይ ድጎማ ይሰጣል። መርሀግብሩ የሚደጎመው በግምጃ ቤት መምሪያ በኩል በሚሰጠው የቤት ክራይ እርዳታ ገንዘብ በኩል ነው።

የእርዳታ ገንዘቡ እስካለ ድረስ፣ ያለባቸውን ዕዳ መክፈል እንዲችሉ እና እስከ ሶስት ወራት የሚያህል የወደፊቱን የቤት ክራይ ወጪ ለመሸፈን እንዲችሉ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች እስከ $12,000 ድረስ የቤት ክራይ እፎይታ ገንዘብ ይሰጣል። የአካባቢው መካከለኛ ገቢ 30% በታች ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ተጨማሪ እርዳታ ሊገኝ ይችላል። የሚሰጦት እርዳታ ማንኛውንም ከአካባቢ፣ ከግዛት ወይም ከፌደራል የሚሰጦትን የቤት ክራይ ድጎማዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል።

**አሁኑኑ ያመልክቱ!**

ለማመልከት መስፈርቱን እናሟላለን ብለው ለሚያስቡ ሁሉም የሞንትጎመሪ ነዋሪዎች እዲያመልክቱ እናበረታታለን።

ተመላሽ አመልካቾች

በሂደት ላይ ያለ ማመልከቻ ላይ መመለስ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎን እዚህ ላይ ጠቅ ያድርጉ።

## ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

### የቤት ክራይ መክፈል ላይ እየታገልኩኝ ነው። ሊገኝ የሚችል ድጋፍ ይኖራል?

ከ COVID ጋር በተያያዘ ኪሳራ የተነሳ የቤት ክራይ መክፈል ላይ ችግር የደረሰብዎት ከሆነ፣ በ DHHS' የመኖሪያ ቤት መረጋጋት አገልግሎቶች በኩል ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል። እባክዎን የኦንላይን ማመልከቻውን እዚህ ላይ ጠቅ ያድርጉ። ኦንላይን ማመልከቻውን በራስዎ ወይም በአከሪያዎ እገዛ በማግኘት ለመሙላት የማይችሉ ከሆነ፣ እባክዎ ድጋፍ ለማግኘት 311 (240-777-0311) ላይ ይደውሉ። ማመልከቻውን መሙላት ላይ ለማገዝ የካውንቲው ሠራተኛ ይደውልሎታል።

### እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

ከ COVID የቤት ክራይ እፎይታ መነሻ ገጽ ላይ በቀጥታ ኦንላይን ማመልከት ይችላሉ። በ COVID ስለደረሰብዎት ተጽእኖ፣ የቤተሰብ ዓባላት፣ ገቢ እና የክራይ መጠን በተመለከተ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ። እባክዎ ደጋፊ ሰነዶችን ለመጫን ይዘጋጁ እና የቤት አከራይዎ መረጃን በቅርብዎ ያኑሩ። እባክዎ ማመልከቻውን ለመሙላት የኢሜይል አድራሻ እንደሚያስፈልግዎ ያስታውሱ። የኢሜይል አድራሻ የሌልዎት ከሆነ፣ እባክዎን አንድ ይፍጠሩ ወይም ከቤት አከራይዎ ወይም ሊያግዝዎት ከሚችል ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር መገናኘትን ከግምት ውስጥ ያስገቡ።

**የኢንተርኔት ግንኙነት የለኝም፣ በተጨማሪም ከተከራየሁበት ቤት ማመልከቻዬን መሙላት ላይ እገዛ ሊሰጡኝ አይችሉም፣ እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?**

**የኢንተርኔት**ግንኙነት የሌልዎት ከሆነ ወይም ማመልከቻውን ለመሙላት ሌላ ቦታ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የካውንቲው ተወካይ ድጋፍ ለመስጠት እንዲደውልሎት ለመጠየቅ 311 (240-777-0311) ላይ መደወል ይችላሉ። MC311 ከእርስዎ መሰረታዊ መረጃን ይሰበስባል እና የመርሀግብሩ ተወካይ ማመልከቻውን መሙላት ላይ ድጋፍ ለመስጠት መልሶ ይደውልሏታልል።

**የመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ ነኝ እና እስካሁን ድረስ ምንም ድጎማ አላገኘሁም። የመጠባበቂያ ዝርዝር ውስጥ እንደሆንኩኝ እንዴት ላውቅ እችላለሁኝ? በድጋሚ ማመልከት ያስፈልገኛል?**

የኦንላይን የመጠባበቂያ ዝርዝር ቅጽ የሞላ ወይም መጠባበቂያ ዝርዝር ላይ እንዲገባ 311 ላይ የደወለ እያንዳንዱ ሰው ሙሉውን ማመልከቻ እንዲሞላ ይጠየቃል። የኢሜል አድራሻ የሚያቀርብ ከሆነ የማመልከቻውን ድህረገጽ በኢሜይል ይላክሎታል። የኢሜይል አድራሻ ያላቀረቡ ከሆነ፣ ማመልከቻው ጋር እንዲገናኙ የካውንቲው ሠራተኛ እርስዎን ያገኞታል። የተሟላ ማመልከቻ መቅረብ አለበት። ሙሉውን ማመልከቻ ለመሙላት ከእኛ ለመስማት መጠበቅ አያስፈልጎትም። የእርስዎ ማመለከቻ በመርሀግብሩ መመሪያዎች መሰረት ይሰናዳል።

**የእኔን ማመልከቻ የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን አለው?**

የለውም፣ ማመልከቻዎችን ለመቀበል ምንም የተቀመጠ ቀነ ገደብ የለም፣ ሆኖም ግን፣ የመርሀግብሩ የእርዳታ ገንዘብ እስካሉ ድረስ ማመልከቻዎችን እንቀበላለን። የእርዳታ ገንዘቡ ውሱን ነው።

**ለ COVID የቤት ኪራይ እፎይታ 3 ምዕራፍ መርሀግብር ብቁ የሚሆነው ማነው?**

ቤተሰቦች የሚከተሉትን ዝቅተኛ የመቀበያ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው:-

- በ COVID-19 የተነሳ የገቢ ማግኘት ችግር የገጠማቸው
- አጠቃላይ የቤተሰቡ ገቢ ከዚህ ቀደም ከነበሩት 30 ቀናት ጋር ሲነፃር ከአካባቢው አማካኝ ገቢ 50% የሆነ ወይም ከዛ በታች
- ቢያንስ ከኦገስት 2020 ጀምሮ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ መሆን።
- አሁን ለሚኖሩበት የቤት አካራይ ቢያንስ $1000 እና ከዚያ በላይ ዕዳ ያላቸው።

**የአሜሪካ ዜጋ መሆን ያስፈልጋል? እንደ ማመልከቻው አካል የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ያስፈልጎታል?**

የሕግ አቋም ማስረጃ አያስፈልግም። ለዚህ መርሀግብር የቀረበው የእርዳታ ገንዘብ በኮንግረስ የጸደቀ ነው ፣ ምክንያቱም የድንገተኛ ጊዜ የሚሰጥ ድጋፍ ስለሆነ፣ የቤተሰብ የሕግ ሁኔታ ሰነድ አያስፈልግም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የማህበራዊ ደህንነት ቁጥሮች አያስፈልጉም።

**AMI ምንድን ነው እና የእኔ ገቢ ከ AMI 50% በታች እንደሆነ እንዴት ላውቅ እችላለሁኝ?**

AMI ማለት የአካባቢው መካከለኛ ገቢ መጠን ነው። የሚሰላው በአካባቢው ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦችን “መካከለኛ” ገቢ በማየት ነው። ከታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ የመጨረሻውን ዓመታዊ ወይም ወርሃዊ ያልተጣራ ገቢ መጠኖች ያቀርባል።

| *የቤተሰብ መጠን* | *የመጨረሻው ዓመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ* ***50% AMI*** | *የመጨረሻው ወርሃዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ* ***50% AMI*** |
|---|---|---|
| 1 | $45,150 | $3,763 |
| 2 | $51,600 | $4,300 |
| 3 | $58,050 | $4,838 |
| 4 | $64,500 | $5,375 |
| 5 | $69,700 | $5,809 |
| 6 | $74,850 | $6,238 |
| 7 | $80,000 | $6,667 |
| 8 | $85,150 | $7,096 |

**የትኛው ገቢ ነው ሪፖርት መደረግ ያለበት እና ይሄንን ለማሳየት ምን ማቅረብ አለብኝ?**

አመልካቾች የቤተሰባቸው ዓባል የእያንዳንዱን ሁኔታ እና በቤተሰቡ ውስጥ ዕድሚያቸው ከ 18 ዓመት በላይ የሆኑ እና የሙሉ ሰዓት ተማሪዎች ያልሆኑ የሁሉም ዓባላቶች የሚያገኙትን ገቢ በትክክል ማቅረብ አለባቸው።

ገቢው የእርስዎ ቤተሰብ የ 2020 ላይ የታክስ ምላሽ ገቢ ወይም ከ 30 ቀናት በፊት ያገኙትን ያልተጣራ ገቢ ሪፖርት ማድረግ ይችላል። ያልተጣራ ገቢ ልክ እንደ ታክሶች እና የመድህን ክፍያዎችን የመሳሰሉ ማንኛውም ዓይነት ቅንስናሾች ሪፖርት ማድረግ አለበት። እነዚህ የሚያካትቱት የሚከተሉትን ሲሆን በእነዚህ ላይ ብቻ አይገደብም፡- የማህበራዊ ደህንነት፣ ጥቅማጥቅሞች/የጡረታ ተቀራጭ፣ የመንግስት ድጎማ፣ የስራ አጥነት፣ የወለድ ክፍያ፣ ወይም የልጅ ማሳደጊያ ተቋራጭ ናቸው። እባክዎ የእርስዎን ያልተጣራ ገቢ ሪፖርት በሚያደርጉበት ሰዓት የኢኮኖሚ ተጽእኖ ክፍያዎች (የፌደራል ወይም የግዛቱ) ወይም የፌደራል የወረርሽኝ የስራ አጥነት ካሳ (ይሄ ተጨማሪ የእርስዎ የስራ አጥነት $300-$600 ክፍያ ነው) እንዳያካትቱ።

ገቢውን ለማረጋገጥ፣ አመልካቾች የእነሱ 2020 የታክስ ምላሽ ወይም በቅርብ ያገኙት የ 30 ቀናት ላይ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው። ይሄ ሊያካትት የሚችለው፡- የክፍያ ደረሰኞች፣ የወለድ ክፍያ መግለጫዎች፣ የስራ አጥነት ድጎማ መግለጫዎች፣ IRS ቅጽ 1040 ለ 2020 ቀን መቁጠሪያ የተሞላ፣ ወይም ቅድመ-COVID እና የአሁኑ ሰዓት በግልጽ የሚያሳይ በራስ-ማረጋገጫ/ ምስክር ወረቀት

**ከኦገስት 2020 ጀምሮ ኪራይ ቤት ከቀየርኩ፣ አሁንም ብቁ ነኝ?**

የኪራይ ሃላፊነት እስካለዎት ድረስ እና ቢያንስ ከኦገስት 2020 ጀምሮ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ እስከሆኑ ድረስ፣ ምንም እንኳን ከዚያ ቀን በኋላ በካውንቲው ውስጥ መኖር ቢጀምሩም።

**ለአንዳንዶቹ የቤተሰብ ወጪዎች ክፍያ እንዲከፍል ከጓደኛዬ ጋር ስምምነት አድርጌአለሁኝ፣ ነገር ግን የራሴ የቤት ክራይ ኮንትራት የለኝም፣ እንደዚህ ሲሆን አሁንም ድጎማ ለማግኘት ብቁ ነኝ?**

ምንም እንኳን መደበኛ ያልሆነ የቤት ክራይ ውል ቢኖሮትም፣ የቤት ክራይ መክፈል ያለብዎ ከሆነ አሁንም ብቁ ኖት። የቤት ክራይ እንዲከፍል የተስማሙት ሰው ማንም ይሁን በወር ምን ያህል መክፈል እንዳለብዎ እና ምን ያህል እንደከፈሉ/ዕዳ እንዳለብዎ በጽሁፍ ያሳውቃል።

**ከቤት ድጎማ መርሀግብር የቤት ክራይ እንድከፍል ድጎማ አግኝቼአለሁኝ (የቤት ምርጫ ቮቸር፣ የቤት ክራይ ድጎማ መርሀግብር፣ ወዘተ)፣ አሁንም ለማመልከት ብቁ ነኝ?**

አዎ። አሁንም ለማመልከት ብቁ ኖት ነገር ግን የእርስዎ ሃላፊነት የሆነው የክራይ ድርሻ ላይ ብቻ ድጎማው ይሰጣል። በተጨማሪም፣ የእርስዎን የድጎማ አቅራቢ ገቢዎት እንደተቀየረ እንዲያሳውቋቸው በጥብቅ እናበረታታዎታለን።

**ምን ያህል ገንዘብ ለማግኘት እችላለሁኝ?**

ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች እስከ $12,000. ዶላር ድረስ ሊያገኙ ይችላሉ። ያልተጣራ ገቢያቸው ከአካባቢው አማካኝ ገቢ 30% ያነሰ የሆኑ ቤተሰቦች ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።እርዳታ ገንዘብ ለክራይ ክፍያ ብቻ የሚሰጡ ናቸው እና ከዚህ ቀደም በማንኛውም የ COVID የክራይ እፎይታ የተገኙ እርዳታ ገንዘብ ወይም ከ COVID ጋር የሚያያዙ የቤት ክራይ እገዛ የተሰጡ የአካባቢው፣ ግዛቱ ወይም የፌደራል እርዳታ ገንዘብ ከግምት ውስጥ ያስገባል።

**ከዚህ ቀደም ድጎማውን አግኝቼአለሁኝ፣ ነገር ግን አሁንም ሙሉ ለሙሉ መክፈል አልቻልኩም ተጨማሪ እገዛ ማግኘት እችላለሁኝ?**

አዎ። ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም የ COVID የቤት ክራይ እፎይታ መርሀግብር ገንዘብ እርዳታ ያገኙ ቢሆንም፣ የመርሀግብሩ ወሰን ድረስ፣ ተጨማሪ ገንዘብ በድጋሚ ለማግኘት ለማመልከት ብቁ ኖት።

**የእኔን ማመልከቻዎችን እንዴት ታስተናግዳላቹህ? ቅድሚያ ለመጣ፣ ቅድሚያ ይሰጣል?**

ማመልከቻዎች ቅድሚያ ለመጣ ቅድሚያ ይሰጣል በሚባል አሰራር አይሰጡም፣ ነገር ግን ከዚያ ይልቅ አካባቢ፣ የቅጥር ሁኔታ እና ከቤት የማስወጣት የፍር

ድ ቤት ማዘዣ ሁኔታ ጨምሮ፣ ብዙ መስፈርቶችን በመጠቀም ይስተናገዳሉ።

DHHS ከ COVID-19 ተጽእኖ፣ የመኖሪያ ቤት ጭንቀት እና ማህበራዊ ወሳኝ ነገሮች ጋር በተያያዘ ሁሉንም መኖሪያ ሰፈሮች ለመገምገም የቤት አልባ መከላከያ ማውጫ አዘጋጅቷል። ማውጫው ማመልከቻዎችን ለማስተናገድ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመለየት ያገለግላል። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ካርታ እዚህ ላይ ማየት ይችላሉ bit.ly/mc-hpi-map።

በተጨማሪም፣ ላላፊት 90 ቀናት ስራ አጥ የሆነ ዓባል ላላቸው ቤተሰቦች ወይም በቅርብ ከቤት እንዲወጡ የፍርድ ቤት ማዘዣ የተሰጣቸው ወይም ከዲስትሪክት ፍርድ ቤት የተፈረደባቸው ቤተሰቦች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

ይሄ ቅድሚያ መስጠት፣ የፊተቻው ቆዳ ጥቁር የሆኑ ማህበረሰቦች በ COVID በከፍተኛ ደረጃ እንደተጠቁ ማስታወቅ፣ በተዛባ ሁኔታ የቤት አልባ ችግር እንደሚያጋጥማቸው፣ እና ከቤት እንዲወጡ የፍርድ ቤት ማዘዣ ወረቀት ሊደርሳቸው የሚችልበት ከፍተኛ ዕድል ስላለ፣ የፍትሃዊነት መነጽር እንዲጠቀም መርሀግብሩ ያስችሉታል።

**የታለሙት "ከፍተኛ ተጽእኖ ያለባቸው" የመኖሪያ ሰፈሮች ውስጥ የማልኖር ከሆነስ?**

የ COVID የቤት ክራይ እፎይታ መርሀግብር 3ኛ ምዕራፍ "ከፍተኛ ተጽእኖ" ያለባቸውን መኖሪያ ቤት ሰፈሮችን ቅድሚያ ይሰጣል። ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች፣ ነገር ግን የታለሙት "ከፍተኛ ተጽእኖ" ያለባቸው መኖሪያ ቤት ሰፈሮች ውስጥ የማይኖሩ የመርሀግብሩ አቅም እስከፈቀደ ድረስ ይጠራሉ።

**ገንዘቡን በቀጥታ አገኛለሁኝ?**

በአብዛኛው፣ ገንዘቡ የእርስዎ የቤት ክራይ ክፍያ ክሬዲት ወደ የቤት አከራይዎ በቀጥታ ይከፈላል። ከቤት አከራይዎ ጋር ለመተባበር ያልቻልን ከሆነ፣ ክፍያው በቀጥታ ለእርስዎ ሊሰጥ ይችላል።

**ምን ዓይነት ሰነዶች ያስፈልጉኛል?**

ማመልከቻዎን ለማጠናቀቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ያስፈልጎታል።

**የፎቶ ያለበት መታወቂያ፡-** ለእያንዳንዱ ዕድሜው አዋቂ ለሆነ ሰው የመንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት ወይም ሌሎች የሚታወቅ ፎቶ መታወቂያ ያስፈልጋቸዋል።

**የመኖሪያ ቤት/አድራሻ ማረጋገጫ፡-** ድጋፍ ለመጠየቅ ማመልከቻ ያስገቡበት አድራሻ ላይ እንደሚኖሩ የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ይገባዎታል። ይሄንን የባንክ መግለጫ፣ ከመንግስት የላከ ደብዳቤ፣ የውሃ፣ የመብራት እና የፍጆታ ክፍያ ደረሰኞች ወይም የእርስዎን አድራሻ የሚያረጋግጡ ሌሎች ሰነዶችን ማቅረብ ይችላሉ።

**የገቢ ማረጋገጫ፡-** በቤተሰብዎ አባል ቁጥር መሰረት የመርሀግብሩን ወሰኖች የማያልፍ ያልተጣራ ገቢ እንዳልዎ የሚያሳይ ሰነድ እና/ወይም የራስ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅቦታል። ይሄ የእስርዎ የ 2020 የታክስ ተመለሽ፣ የክፍያ ማረጋገጫ ወረቀት፣ ከቀጣሪዎ የሚሰጥ ደብዳቤ፣ የስር አጥነት ደብዳቤ ወይም የራስ ማረጋገጭ ምስክርነት ሊሆኑ ይችላሉ።

**የክራይ ማረጋገጫ።** የእርስዎን የክራይ ሃላፊነት፣ የክፍያ ታሪክ እና ያለብዎን ዕዳ የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ያስፈልግዎታል። ይሄ በክራይ መዝገብ፣ የክራይ ውል፣ ወይም ሌሎች ሰነዶችን በማጣመር የሚፈለገውን ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።

**የቤት አከራይ ሰነድ፡-** የእርስዎ የቤት አካራይ የካውንቲው የቤት አከራይ ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ መመዘገብ አለበት እና የቤት አካራይነት የሚያሳይ፣ ወርሃዊ የክራይ መጠን እና ምን ያህል እንደሚከፈል ጨምሮ የክራይ መረጃ ሰነድ ማቅረብ አለበት።

**በቀጣሪዬ የተሰጠ ደብዳቤ የለኝም፣ ራሴን ችዬ ነው የምሰራው፣ ወይም መደበኛ የሆነ የስራ ሰዓት የለኝም። ገቢዬን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ አለብኝ?**

የማመልከቻ ፖርታሉ ላይ የራስ ማረጋገጫ መጫን አለብዎ። ከ COVID በፊት የእርስዎን ቅጥር/ገቢ መረጃ እና የአሁኑን የቅጥር/ገቢ መረጃ ማካተት አለበት።

**ከመጀመሪያው የ HHS COVID የቤት ክራይ እፎይታ መርሀግብር ወይም የዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከሌላ የቤት ክራይ መርሀግብር አስቀድሜ ገንዘብ ተቀብዬአለሁኝ። ተጨማሪ ገንዘብ በድጋሚ ማመልከት አለብኝ?**

በ DHHS COVID የቤት ክራይ እፎይታ መርሀግብር፣ በግዛቱ የሚደገፍ የመኖሪያ ቤት እፎይታ መርሀግብር፣ HOC COVID የቤት ክራይ ድጎማ መርሀግብር ወይም ከማንኛውም ሌላ መርሀግብር የቤት ክራይ ድጎማ አስቀድመው ያገኙ ከሆነ፣ የ COVID የቤት ክራይ እፎይታ ገንዘብ ለማግኘት ብቁ **ኖት።**

ለሁሉም ሌሎች HHS የቤት ክራይ ድጎማ መርሀግብሮች፣ በዚህ የሕዝብ የጤና ድንገተኛ ጊዜ ላይ መደበኛው የ 12-ወር ጥቅማጥቅም የመጨረሻው መጠን እንዲሻር ተደርጓል። ሌሎች የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ፣ አሁንም ቢሆን ጥቅማጥቅም ማግኘት ይችላሉ።

**ይሄንን ገንዘብ የ2021 ታክሶቼ ላይ ሪፖርት ማድረግ አለብኝ?**

አይ፣ በአብዛኛው፣ ገንዘቡ የእርስዎ የቤት ክራይ ክፍያ ክሬዲት ወደ የቤት አካራይዎ በቀጥታ ይላካል። የቤት አካራዮች የቤት ክራይ ክፍያውን እንደ የክራይ ገቢ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

**ድጎማውን መቀበል የመንግስት ጥገኛ ተደርጎ ሊያስቆጥር ይችላል?**

DHHS የመንግስት ጥገኛነት ላይ የሕግ ስልጣን የለውም። እንደዚህ ዓይነት ስጋት ያለዎት ከሆነ የሚከተሉትን የሕግ ግብዓቶች እንዲያገኙ ይመከራሉ፦

- ስደተኛ ቤተሰቦችን መጠበቅ
- ጊልክረስት ማዕከል
- ሜርላንድ የጤና ግንኙነት
- አንድ አገር AAPI-የኤዥያ አሜሪካ እና ፐስፊክ አይላንደር (በስፓኒሽኛ እና በብዙ የኤዥያ ቋንቋዎች ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች)
- ዕድሚያቸው ለገፉ ፍትሕ

**እስካሁን ድረስ የቤት ክራይ መክፈል ችዬ ነበር፣ ነገር ግን የሚቀጥለው ወር ላይ መክፈል የሚችል አይመስለኝም፣ እገዛ ማግኘት እችላለሁኝ?**

እንደ ዕድል ሆኖ፣ ይሄ መርሀግብር የሚሰጠው የቤት ክራይ ላይ ቢያንስ $1000 ዕዳ ላለባቸው መኖሪያ ቤቶች ብቻ ይሰጣል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ራስዎን ያገኙ ከሆኑ፣ እባክዎን በዚያ ጊዜ ላይ ያመልክቱ።

**ይሄንን ገንዘብ መልሼ መክፈል አለብኝ?**

አይ። ይሄ ብድር አይደለም። ለአገሪቱ መልሰው መክፈል አያስፈልግዎትም።

**የቤት አከራዬ ሁሉንም ሙሉ ለሙሉ የማልከፍል ከሆነ በፍጥነት ከቤት ለቅቄ መውጣት እንዳለብኝ ነገረኝ። የት ለመሄድ እችላለሁኝ?**

የፍርድ ቤት ከቤት ማስወጫ ማዘዣ ወረቀት የያዘ ፖሊስ መኮንን ብቻ ያንን ማድረግ ይችላል። እባክዎ የቤት አከራዮች እና ተከራዮች ጉዳዮች ላይ በ 240-777-0311 እና የፖሊስ መምሪያውን የድንገተኛ ጊዜ ያልሆነ ስልክ ቁጥር በ 301-279-8000 ደውለው ያግኙ። ተጨማሪ መረጃ በ የመኖሪያ ቤቶች እና የማህበረሰብ ጉዳዮች መምሪያ (Department of Housing and Community Affairs) (DHCA) COVID-19 ድረገጽ ላይ ያገኛሉ።

**ከቤት የማስወጫ የፍርድ ቤት ችሎት መጥሪያ ወረቀት ደርሶኛል፣ ምን ማድረግ አለብኝ?**

የፍርድ ቤት የክስ ሂደቶች ላይ እንዲሳተፉ እንመክሮታለን ምክንያቱም ከ COVID ጋር የሚያያዝ ከቤት የማስወጫ ቀን እንዲዘገይ የሚያደርግ ፍርድ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እባክዎ በዚህ ላይ የሚገኘውን መረጃ ይመልከቱ DHCA COVID-19 ድረገጽ።

**እኔ የቤት አከራይ ነኝ እና የእኔ ተከራይ ብቁ ነው ብዬ አስባለሁኝ፣ ምን ለማድረግ እችላለሁኝ?**

እባክዎን የማመልከቻውን የቤት አከራይ ክፍል ይሙሉ እና የእርስዎ ተከራይ የእነሱን የማመልከቻ ክፍል እንዲሞሉ ያግዟቸው።

**የቤት አከራዩ ማቅረብ ያለበት ሰነዶች ምንድን ናቸው?**

ሁሉም የቤት አከራዮች ከካውንቲው ክፍያ ለመቀበል የካውንቲው ማዕከላዊ የቤት አከራይ ምዝገባ ስርዓት መመዝገብ አለባቸው። በተጨማሪም የእርስዎ ተከራይ በወር ምን ያህል እንደሚከፍልዎ፣ ምን ያህል እንደከፈሉ እና ምን ያህል ዕዳ እንዳለባቸው የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ያስፈልጎታል። ለዚህ ክፍል ማንኛውም እየተሰጠ ያለ ድጋፍ ይፋ ማድረግ አለብዎ።

**ይሄንን ድጎማ ለመቀበል የቤት አከራዩ ማሟላት ያለበት መስፈርቶች አሉ?**
የቤት አከራዩ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ መስማማት አለበት፡-

- የዘገዩ ክፍያዎች፣ ቅጣቶችን፣ ወለድ እና የሕግ ክፍያዎችን መሻር አለበት፣
- ማንኛውም በቅርብ የተገኙ ከቤት ማስወጫ የፍርድ ቤት መዛዣዎችን መሰረዝ እና የ COVID የቤት ክራይ እፎይታ መርሀግብር ገንዘብ እየተቀበሉ እያለ እና ከእፎይታ ጊዜ በኋላ ለ 30 ቀናት ያህል በፍርድ ቤት ማዘዣ ከቤት ለማስወጣ አለመክሰስ (ይሄ በደህንነት ምክንያት የየክራይ ውል ጥሰትን አያካትትም)፣
- የቤት ክራይ ውሉ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የቤት ክራይ ውሉ ለ 90 ቀናት ያህል እንዲታደስ ማድረግ፣ እና
- ለ DHHS ማሳወቅ እና ተከራዩ ለቆ የወጣ ከሆነ የቀሩትን ገንዘቦች መመለስ።